

# ‹‹ሴቶች ሁልጊዜ የተሻለ ሠርተንና ልዩ ነገር ይዘን ካልወጣን በስተቀር አስቸጋሪ ነው››

14 Apr, 2017 By ዳዊት ታዬ 0 Comments

**ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ፣ የእናት ባንክ የቦርድ ሊቀመንበርና የሕግ ባለሙያ**

*ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ ተወልደው ያደጉት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ ነው፡፡ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉትም በአሶሳ ከተማ ነው፡፡ ከፍተኛ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ወስደዋል፡፡ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በኢንተርናሽናል ሪሌሽንስ አግኝተዋል፡፡ ከአሶሳ ወጥተው አዲስ አበባ ከተማን ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጡት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ለመማር ተመድበው በመጡበት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙ በኋላ መጀመሪያ ወደ ሥራው ዓለም የቀላቀሉት ንግድ ሚኒስቴር ነው፡፡ ንግድ ሚኒስቴርን ከለቀቁ በኋላ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው ሠርተዋል፡፡ ብዙም ያልገፉበትን የዳኝነት ሥራ ለቀው በሕገ መንግሥት ኮሚሽን ውስጥ ሠርተዋል፡፡ በተለይ በሕገ መንግሥት ኮሚሽን መሥራታቸው ይበልጥ የሚታወቁበትን የሴት የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርን ለመመሥረት ዕድል ያገኙበት ነበር፡፡ እንደ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ያሉ ድርጅቶችም ሠርተዋል፡፡ አሁን ደግሞ በ11 ሴቶች አደራጅነት የተቋቋመው የእናት ባንክ ቦርድ ሊቀመንበር ሆነው እያገለገሉ ነው፡፡* ***ዳዊት ታዬ*** *ከሥራቸውና ከግል ሕይወታቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ አነጋግሯቸዋል፡፡*

***ሪፖርተር፡- ወ/ሮ መዓዛ ቀድሞ የሚታወቁት የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር በመመሥረትና በዚያ ላይ በመንቀሳቀስ ነው፡፡ ቆይተው ደግሞ ወደ ፋይናንስ ኢንዱስትሪው ገብተዋል፡፡ እንደሚታወቀው እናት ባንክን ከሌሎች አጋርዎችዎ ጋር በመሆን ማቋቋም ችላችኋል፡፡ እንዴት ወደ እዚህ ዘርፍ ገቡ? የእናት ባንክ አመሠራረትስ የተለየ ታሪክ አለው?***

**ወ/ሮ መዓዛ፡-** እኔ የቢዝነስ ሰው አይደለሁም፡፡ የቆየ ልምዴም ብዙ ከቢዝነስ የራቀ ነው፡፡ የእናት ባንክ መመሥረት በአጋጣሚ ነው፡፡ በአንድ ወቅት ሸራተን አዲስ ስብሰባ ተጠራን፡፡ አንድ የሴቶች ድርጅት ያዘጋጀው ስብሰባ ነው፡፡ የስብሰባው አጀንዳም ‹‹ሴቶች ቢዝነስ የሚሠሩበት ቦታ የላቸውም፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ችግር ነው›› የሚል ነበር፡፡ በስብሰባው ላይ ከጎኔ ወ/ሮ ሣራ አበራ ነበረችና፣ ‹‹ሴቶች እኮ ብር ቢኖራቸው ቦታ መከራየት፣ ቦታ መግዛት ይችላሉ፡፡›› አለች፡፡ ከዚያም የዚህ ስብሰባ አጀንዳ መሆን የነበረበት ሴቶች ፋይናንስ እንዲያገኙ ምን መደረግ አለበት መሆን ነበረበት አለች፡፡ እስቲ ለሴቶች የሚያግዝ ባንክ ቢኖር ብላ ሐሳቧን ሰነዘረች፡፡ እኔንም እንዳስብበት ጠየቀችኝ፡፡ ከዚያም ስብሰባውን አቋርጠን ወጣንና ሒልተን ሄደን ወይን እየጠጣን ስለሴቶች ባንክ ማውራት ጀመርን፡፡ በነጋታውም ከዚያም በኋላ ስለሴቶች ባንክ መቋቋም መወያየት ጀመርን፡፡ ሐሳባችን ሁሉ እሱ ሆነ፡፡ ሦስት አራት ወራት ይህንኑ ጉዳይ እያነሳንና እየተወያየንበት ብንቆይም፣ መሀል ላይ ግን ሥጋት የሚፈጥሩብንም ነገሮች ነበሩ፡፡

***ሪፖርተር፡- ለምን? የሥጋቱ ምንጭ ምንድነው?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** ምክንያቱም የእኛ ሐሳብ ጥሩ ቢሆንም ገንዘብ የለንም፡፡ ባንክ የሚያቋቁሙት ከፍተኛ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ናቸውና ይኼ ነገር ይሳካልን ይሆን አይሆን ብለን ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ነገሩን ስናወጣ ስናወርድ ቆየን፡፡ እዚህ ውስጥ እከሌን ብናስገባ እከሊትን ብንጠራ እያልን ከእኛ ጋር ሊሠሩ ይችላሉ ያልናቸውን ሴቶች ሰበሰብን፡፡ እኔና ሣራ ከእኛ ጋር ሊሠሩ ይችላሉ ያልናቸው ሴቶች ማሰብ ጀመርን፡፡ ያሰብናቸውን አሥራ አንድ ሴቶች ጠራን፡፡ ነገር ግን ይህንን እስክናደርግ ድረስ እኔና ሣራ ስለነገሩ ሰዎችን ከማማከርና ከማወያየት ውጪ ምንም የተጨበጠ ሥራ አልሠራንም፡፡ አሥራ አንዳችን በነገሩ ተስማምተን ወደ ተግባር ለመሸጋገር ወሰንን፡፡ አክሲዮን መሸጥ ገባን፡፡ በመሥራችነት የተሰባሰቡት አሥራ አንዱ ሴቶች ጠንካሮች ነበሩ፡፡ የሚገርምህ ነገር አሥራ አንዱም እያንዳንዳቸው በራሳቸው ብዙ ታሪክ ያላቸው ናቸው፡፡ በተለይ በቢዝነሱ ዓለም ብዙ የለፉ፣ የደከሙና የሠሩ ናቸው፡፡ እንደ ምሳሌ የሚታዩም ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ካለን ልምድ አንፃር ተጋግዘንና ተበረታተን ባንኩን ለማቋቋም እስከ መጨረሻው በመሄዳችን ተሳክቶልናል፡፡ ውጤቱ በጋራ የሠራነው ሥራ ነው፡፡

***ሪፖርተር፡- እናት ባንክን ለማቋቋም ግን ብዙ ውጣ ውረዶች እንደነበሩ አውቃለሁ፡፡ በመካከል ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች እንዳጋጠሙዋችሁም አስታውሳለሁ፡፡ ችግሩ ምን ነበር?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** ብዙ ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡ ዋናው ፈተና አክሲዮን እየሸጥን በነበረበት ወቅት የገጠመን አንዱ ነው፡፡ ባንኩን ለማቋቋም የሚያስችለንን ካፒታል ለመሙላት የምናደርገው የአክሲዮን ሽያጭ ሄዶ ሄዶ 13 ሚሊዮን ብር ላይ ደርሶ ቀጥ አለ፡፡ ከዚህ ከፍ ለማድረግ ፈተና ሆነ በቃ፡፡ ቆምን፡፡ የሚፈለገው እስከ 100 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ነገር ግን ከ13 ሚሊዮን ብር በላይ ለመሄድ ተቸገርን፡፡ ምን እናድርግ እያልን ሳለ ከእኛ አንዷ የሆነችው ወ/ሮ ሒሩት አላምረው ጎበዝ ሴልስ ብዙ ሰው ታውቃለች፡፡ እርሷ የምታውቀውን ሰው እንዲመጣ አድርጋ በፕሮጀክት ማኔጀርነት እንዲቀጠር አድርገን የምንፈልገውን ካፒታል በአምስት ወራት ውስጥ ሞላን፡፡

***ሪፖርተር፡- እንግዲህ አነሳሳችሁ የሴቶች ባንክ በማቋቋም ሴቶችን ለመደገፍ ነው፡፡ ደግሞ ልክ እንደ እናንተው ‹‹ሔዋን›› የሚል ስያሜ ያለው ሌላ የሴቶች ባንክ እየተቋቋመ መሆኑ አስደንግጧችሁ ነበርም ይባላል፡፡ እናት የሚለውስ ስያሜ እንዴት ወጣ?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** እዚህ ላይ የሚገርም ታሪክ አለ፡፡ እኛ ይህንን ባንክ እውን ለማድረግ ጊዜ ወስዶብናል፡፡ ይህንን ነገር ይዘን ለሕዝብ ስንቀርብ ያስኬደናል ወይ? እንወጣዋለን ወይ? እያልን ብዙ ወራት ፈጅተናል፡፡ በመካከል ግን ሌሎች የሴቶች ባንክ ለማቋቋም እየተንቀሳቀሱ ነው የሚል መረጃ ደረሰን፡፡ ሁለት የሴቶች ባንክ ሊቋቋም ይችላል፡፡ ነገር ግን ለእኛ የታየን ይህ ከሆነ ሕዝብ ብዥታ ውስጥ ሊገባ ነው፡፡ ሁለታችንም እንዲህ ካደረግን ሕዝቡን ማደናበሩ ብቻ ሳይሆን ሁለታችንም ልንወድቅ እንችላለን የሚል ሥጋት ፈጠረብን፡፡ ነገር ግን እኛ መፍጠንና ቶሎ ቶሎ መራመድ አለብን ብለን ቀጠልን፡፡ እኛ ያኔ ስንነሳ የባንኩን ስያሜ ‹‹Women’s Bank of Ethiopia›› ነበር ያልነው፡፡ በዚህ ስያሜ ንግድ ሚኒስቴር ልናስመዘግብ ሄድን፡፡ ነገር ግን ያኔ አቶ ግርማ ብሩ ነበሩና ‹‹Women’s Bank of Ethiopia›› አይሆንም ጀኔሪክ (የወል) ስለሆነ አይሆንም ሲሉን አዘንን፡፡ ምክንያቱም የሴቶች ባንክ የሚለውን ነገር ፈልገነው ነበር፡፡ ከዚያ ስሙን ለመለወጥ ሌላ ስያሜ ለማግኘት ፍለጋ ገባን፡፡ ሁላችንም ብዙ አሰብን፡፡ አሁንም ከመካከላችን አሁንም ሒሩት ስም ሊያወጣ ይችላል ብላ ላሰበችው ሰው ስልክ ደውላ ይሆናል ብሎ የነገራትን ይዛልን መጣች፡፡ ‹‹እናት ኢትዮጵያ›› ነበር ያሉት፡፡ ይህንን የሰሙ አንዳንዶቹ ውይ ይኼማ የደርግ ስያሜ ይመስላል አሉና ባይሆን እናት በሚለው እንርጋ ተባለ፡፡

***ሪፖርተር፡- እናት የንግድ ባንክ ቢሆንም በግልጽ ያስቀመጣችሁት የተለየ አካሄድ እንዲኖረው ተፈልጓል፡፡ በፋይናንስ ሴቶችን ማገዝ ነው፡፡ እስኪ ስትነሱ የያዛችሁትንና የተነሳችሁበትን ዓላማ ያስታውሱኝ?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** እንደ ማንኛውም ንግድ ባንክ ሠርቶ ማትረፍ አለበት፡፡ የባለ አክሲዮኖች ገንዘብ ነው፡፡ ነገር ግን አሥራ አንዳችን ንግድ ባንክ ለማቋቋም አልነበረም የተነሳነው፡፡ ይህ ፍላጎት አልነበረንም፡፡ የተሰባሰብንበት ዋነኛ ዓላማ ሴቶችን በኢኮኖሚ ለማብቃት የሚያስችል፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ለሴቶች መሣሪያ ሊሆን የሚችል የፋይናንስ ተቋም ለመፍጠር ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ባንኩ በአሥራ አንድ መሥራች ሴቶች መቋቋሙና 64 በመቶ ሴቶች መሆናቸው፣ ከ65 በመቶ በላይ የቦርድ አባል መሆናቸው፣ ከ50 በመቶ በላይ ሠራተኞቹ ሴቶች መሆናቸው በዓለም ላይ ልዩ አድርጎታል፡፡ ስለሌላ ነገር ሳንነጋገር ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሴቶች አይደለም ባንክ ማይክሮ ፋይናንስም ማቋቋም አልቻሉም፡፡ ሴቶች የሚታወቁት ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት 300 እና 400 ብር በመበደር ነበር፡፡ እዚያ ድረስ ነበር የተሰመረላቸው ቦታ፡፡ ይህ ግን የእናት

ባንክ መቋቋም ይህንን ሁሉ ለወጠ፡፡ ብዙ ሰዎች ደግሞ እምነትም አልነበራቸውም፡፡ የትም አይደርሱም እስከ መባል ደርሰን ነበር፡፡ እንዲያውም የታወቁትና የፋይናንስ ዘርፍ ባለሙያ የሆኑት አቶ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ደግፈውን ነበርና እሳቸው እንኳን በጣም እያበረታቱን ነው ብለን ሌሎቹን ድጋፍ ስንጠይቅ፣ ‹‹አቶ ኢየሱስ እየደገፏችሁ ያሉት የትም አትደርሱም ብለው ነው፤›› ብለው የቀለዱብንም አሉ፡፡ ግን ሁሉ ነገር ተሳካ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ይህ ባንክ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱለት የሚችሉ ብዙ ነገሮች አሉት፡፡ ትኩረት አድርገው ሴቶች ከሠሩና ከተባበሩ ትልቅ ነገር መሥራት እንደሚቻል ነው፡፡ እኛ አሁን ትልልቆች ነን፡፡ ዕድሜያችን ትልቅ ነው፡፡ ከእኛ በኋላ ላሉት ምሳሌ ይሆናል ብለን ነው የምናስበው፡፡ በነገራችን ላይ  በተለይ ሴቶች ሁልጊዜ የተሻለ ሥርተንና ልዩ ነገር ይዘን ካልወጣን በስተቀር አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምሳሌ በሌላ አገር ጥቁር ከሆንክ በጣም የተለየ አፈጻጸም ከሌለህና አፈጻጸምህ እንደ ሌላው ሰው ከሆነ በልዩነት ነው የምትፈረጀው፡፡ ወይም ችሎታ የለህም ተብለህ ነው የምትታየው፡፡ ስለዚህ ሴትም ተሁኖ የተለየ ውጤት ይጠበቃል፡፡ ሥራን በራሳችን መንገድ ነው ማስኬድ ያለብን፡፡ መሥራት ነው፡፡ የምናስመዘግበው ስኬት ደግሞ የሌላውን ዓይን ለመሙላት ሳይሆን በራሱ ማሳየት አለበት፡፡

***ሪፖርተር፡- ሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማጎልበትና ለመደገፍ ካላችሁ የተነሳችሁበት ዓላማ እየተሳካ ነው? ባሰባችሁት ደረጃ ለሴቶች ፋይናንስ ማቅረብ ችላችኋል? ሴቶችን ማበደር ችላችኋል?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** አጠቃላይ የባንኩን ታሪክ ካነሳህ በመጀመሪያው ዓመት አትራፊ ሆኖ የወጣ ባንክ ነው፡፡ የግል ባንኮች በሙሉ ወደ ትርፍ ለመግባት ሁለት ሦስት ዓመት ይወስድባቸዋል፡፡ እኛ ግን በመጀመሪያው ዓመት ነው ያተረፍነው፡፡ ይህንን ካነሳህ አደራጆች እንደ አደራጅነታችን አምስት ሳንቲም አልተከፈለንም፡፡ ከመሥራቾቹ ሦስቱ በባንኩ ቦርድ ውስጥ ገብተናል፡፡ ጥሩ ቦርድ ስለነበረም ከማኔጅመንቱ ጋር ሆነን በጥንቃቄ በመሥራታችን በመጀመርያው ዓመት አትርፈናል፡፡ ሴቶችን በተመለከተ እናት ባንክ ሴቶችን የሚደግፍ ልዩ ፕሮግራሞች አዘጋጅቶ እየሠራ ነው፡፡ ይኼ ግን በምንፈልገው ፍጥነት  አልሄደም፡፡

***ሪፖርተር፡- ለምን?***

***ወ/ሮ መዓዛ፡-*** ምክንያቱም ባንካችን ሁለት ዓላማ ይዞ ስለሚሄድ ነው፡፡ አንደኛው ለባለ አክሲዮኖችን ትርፍ ማስገኘትና ቀጣይ መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሴቶችን አጀንዳ ይዞ መሄድ አለበት፡፡  ሁለቱ ጉዳዮች በአንድ በኩል የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ይህንን ለማሳካት በተለይ የሴቶችን የፋይናንስ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥልን እንድንችል፡፡ ይህንን ለመድረስ ቀጥታ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ የሆነ አንድ ዲቪዥን አቋቁመናል፡፡ ይህ ዲቪዥን የሴቶችን የፋይናንስ አገልግሎት የሚያዳብር ነው፡፡ ለምሳሌ ጠቅላላ ጉባዔው ወይም ባለ አክሲዮኖች ከባንኩ ዓመታዊ ትርፍ አምስት በመቶ የሚሆነውን ‹‹ሪስክ ፈንድ›› እንዲገባ በመወሰን፣ ለሴቶች ብድር የሚመቻችበትን መንገድ መቀየስ አንዱ ነው፡፡

ይህም አንድ ሴት ጥሩ የሆነ የቢዝነስ ሐሳብ ያላት ሆና ይህንን ሐሳቧን መሬት ላይ ለማውረድ የሚያስችል አቅም ከሌላት ወይም ብድር ለማግኘት ለማስያዣ የሚሆን ንብረት ከሌላት፣ ለብድር ማስያዣ የሚሆነውን ከፈንዱ መጠቀም ነው፡፡ እንዲህ ባለው አሠራር ለ17 ሴቶች በአማካይ ሦስት መቶ ሺሕ ብር ብድር ሰጥተን እንዳሉት ‹‹ፕሮግራም እየሠሩ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር እየሠራን ነው፡፡ ገጠር ላይ አቅም ለሌላቸው እስካሁን ለ500 ሴቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ዩኤስኤይድና ሲዳ የአሥር ሚሊዮን ብር ‹ጋራንቲ ሌተር› ሰጥተውናል፡፡ ይህንን ብር በከፊል እንደ ዋስትና በመጠቀም ለበርካታ ሴቶች ብድር ለመስጠት ዝግጅት ላይ ነን፡፡ ሴቶችን በፋይናንስ በመደገፍ ረገድ እያደጉ የመጡ ሥራዎች አሉ፡፡ ሴቶችን ተጠቃሚ በማድረጉ ረገድ ባንካችን የሚሠራው ሌላው ነገር በየጊዜው ከዩኒቨርሲቲ የሚወጡ ተማሪዎችን እያሠለጠንን ወደ ሥራ እናስገባለን፡፡ በዚህ መንገድ ከተቀጠሩት 150 ከሚሆኑት ውስጥ 120 ሴቶች ናቸው፡፡